የባህልና ቱሪዝም
ሚኒስቴር

# የቅርስ አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 480/2013

ህዳር 2006 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 480/2013

## የባህልና ቱሪዝም

## ሚኒስቴር

## የቅርስ አሰባሰብ
## መመሪያ

ቅርሶች በአግባft ተጠብቀው ለሣይንስና ለምርምር፣ ለኢኮኖሚያዊ ልማትና ለባህል ዕድገት የጎላ አስተዋፅዖና ጠቀሜታ ሊያበረክቱ በሚችሉበት መንገድ በባህል ተቋማትና ማዕከላት በማሰባሰብ ማደራጀት ተገቢ በመሆኑ፣

ምትክ የሌላቸውንና የሕዝቦችን ማንነት ዓይነተኛ መገለጫዎች የሆኑ የታሪክና የባህል ቅርሶችን በማሰባሰብ ከማንኛውም ዓይነት ጉዳትና ጥፋት በማዳን ለትውልድ ማቆየት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ሀገራዊ ጉዳይ ስለሆነ፣

የአንድን የቅርስ ስብስብ ማዕከል የቅርስ ክምችት በተገቢው ዓይነትና መጠን በማሳደግ ሀገራዊ ደረጃውን እንዲጠብቅ ለማድረግ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የተጠናከረ የቅርስ ማሰባሰቢያ ሥርዓት መዘርጋትና የአፈፃፀም ስልት በመቅረፅ ሥራ ላይ ማዋል በመሆኑ፣

የቅርስ ክምችቶች ስፋት ባለው ብሔራዊ ተዋፅዖ ላይ ተመሥርተው ቅርሶችን ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የቅርስ አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 480/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ *መመሪያ* ውስጥ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 ነው፡፡
2. በአዋጁ አንቀፅ 3 የተሰጠው ትርጓሜ ለዚህም መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል
3. **"ቅርስ ማሰባሰብ"** ማለት በቅርስ ስብስብ ማዕከሎች የቅርስ ማሰባሰቢያ ሥርዓት መሠረት የተለያዩ ቅርሶችን ማሰባሰብና ወደ ስብስብ ክፍል ማስገባት ነው፣
4. **"የስብስብ ማዕከል"** ማለት የተለያዩ ቅርሶች ተሰባስበው የሚጠበቁበት፣ እንክብካቤ የሚደረግበት፣ የሚደራጁበትና ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ዝግጁ የሚሆኑበት ክፍል ነው፡፡

3. **"የሥነ ጥበብ ቅርስ"** ማለት አንድ ማኅበረሰብ ሁለንተናዊና ባህላዊ እሴቱን ፣ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴውንና ማንነቱን የሚያይበት፣ የሚያስተውልበትና ራሱን የሚገልፅበት ሕይወት በሌለው ቁስ ላይ ሕይወት የሚፈጠርበት ቅርስ ነው፡፡
4. **"ታሪካዊ ቅርስ"** ማለት በአንድ ኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የነበረውን ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ሥነ ጥበባዊ ሁኔታዎችን በማንፀባረቅ ለቀጣይ ጥናት በመረጃነት የሚያገለግል ከፍተኛ ታሪካዊ ፋይዳ ያለው ቅርስ ነው፡፡

6. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፣
7. **"ባለሥልጣን"** ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
8. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሀገራችን የሚገኙ ቅርሶች ወደ ስብስብ ማዕከሎች የሚገfiበትን ሥርዓት ወጥ በሆነ መልኩ እንዲዘረጋ ለማስቻል ነው፡፡

## 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ቅርሶችን ለጥናትና ለምርምር፣ ለጉብኝት፣ ለባህል ልውውጥ ወይም ለመሰል ዓላማዎች በሚያሰባስfi፣በሚጠብቁና በሚንከባከfi በሀገሪቱ በሚገኙ የቅርስ ማዕከሎች ሁሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ቅርሶችን

5. **ስለማሰባሰብ**

**መሠረት**

ቅርስ በስጦታ፣ በግዥ፣ በአደራ፣ በውሰት፣ በውርስ፣ በልውውጥ፣ በጥናትና ምርምር እና ከውጭ ሀገር እንዲመለሱ በማድረግ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

6. **ቅርስን በስጦታ ስለማሰባሰብ**

1. በራሳቸው ፍላጎት ሊለግሱ ከሚችሉ አካላት ወይም ግለሰቦች ቅርስ በስጦታ ሊሰባሰብ ይችላል፡
2. የስብስብ ማዕከሉ ቅርሶችን በስጦታ ሊያበረክቱ የሚችሉ አካላትን ለማበረታታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሠራል፤
3. የስብስብ ማዕከሉ በስጦታ የሚያገኘውን ቅርስ፣ የቅርስነት መሥፈርት ማሟላቱንና መረጃ ያለው መሆኑን በቅድሚያ በባለሙያ በማረጋገጥ፣ መረጃውንም በቅርስ መረከቢያ ቅፅ ላይ በዝርዝር በማስፈር ይረከባል፣
4. ቅርስን በስጦታ የሚያበረክት አካል ከተረካቢው የምሥጋና ሠርተፍኬት ይሠጠዋል፡፡
5. በስጦታ ወደ ስብስብ ማዕከል የሚገባ ቅርስ ሕጋዊ የስጦታ አፈፃፀም ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ክፍያ ወይም መተኪያ ሊጠየቅበት አይችልም፡፡
6. በጊዜያዊ ዓውደ ርዕይ ለዕይታ የቀረበና በሥራው ባለቤት የሚበረከት የሥራ ውጤት ወደ ስብስብ ማዕከል እንዲገባ ይደረጋል፡፡

7. **ቅርስን በግዥ ስለማሰባሰብ**

በአዋጁ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ

1. የታሪካዊ ፤ የሥነጥበብ፣ የኢትኖግራፊና የንፅፅራዊ ሥነ አካል /ኮምፓራቲቭ አናቶሚ/ቅርሶች የቅርስነት እሴት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በግዢ ሊሰባሰብ ይችላል፡፡
2. ቅርሶች የተገልጋዮችንና የስብስብ ማዕከሎችን ፍላጎት በማጥናት በግዥ እንዲሰባሰብ ይደረጋል ፡፡

3. የታሪክና የባህል ቅርስ ካለው ልዩ ይዘትና ባህርይ የተነሳ ግኘቱ በመንግሥት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 51 ንዑስ 1 ፊደል ሸ በተመለከተው መሠረት ያለጨረታ ይፈፀማል፡፡
4. ቅርስ በሽያጭ የሚያቀርብ ግለሰብ ወይም ተቋም ባለቤትነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲጠየቅ የማቅረብ ግደታ አለበት፡፡
5. ቅርስን በአደራ ያስቀመጠ ባለይዞታ የአደራ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት መሸጥ ከፈለገ የስብስብ ማዕከሉ ሊገዛ ይችላል፤

8. <u>ቅርስን በአደራ ስለማሰባሰብ</u>

1. የስብስብ ማዕከሎች ከቅርስ ባለይዞታዎች ጋር በሚያደርጉት ሥምምነት መሠረት በአደራ ተረክበው ለተወሰነ የጊዜ ገደብ ቅርስ ሊሰባሰብ ይችላል፤
2. የስብስብ ማዕከሉ የአደራ ሰጪውን ማመልከቻ በመቀበል ቅርሱን ከቦታው ሄዶ በማየት ስለነባራዊ ሁኔታው መረጃ ይሰበስባል፤
3. ማንኛውም የቅርስ ባለይዞታ በስብስብ ማዕከሉ ቅርስን ማስቀመጥ የሚችለው ከ5 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሲሆን፣ በአደራ ያስቀመጠውን ቅርስ መውሰድ የሚችለውም ከማዕከሉ ጋር የተስማማበትን የጊዜ ገደብ ሲያጠናቅቅ ብቻ ነው፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ቅርስን በአደራ ማስቀመጥ የሚፈልግ የቅርስ ባለይዞታ ሥምምነቱን ለ2 ዓመት ብቻ ማራዘም ይችላል፡፡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ካላደሰ የስብስብ ማዕከሉ ቅርሱን ሊወርስ ይችላል፤
5. ባለሥልጣኑ የስብስብ ማዕከሉ በአደራ ስለሚያስቀምጣቸው ቅርሶች ብዛትና ዓይነት መመዘኛ ያወጣል፤
6. የስብስብ ማዕከሉ ማንኛውንም ዓይነት ቅርስ በአደራ ሲቀበል በሥምምነት ቅጽ ላይ መረጃዎቹንና የአደራ አስቀማጩን መብትና ግዴታ በዝርዝር በሚገልፅ ውል ከአስረካቢው ወገን ጋር በመፈራረም ይረከባል፤
7. የስብስብ ማዕከሉ በአደራ የሚቀበለውን ቅርስ ከአደራ አስቀማጩ ጋር በሚደረግ ሥምምነት ላይ በመመሥረት ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

9. <u>ቅርስን በውሰት ስለማሰባሰብ</u>

1. ቅርስ ለዓውደ ርዕይ፣ ለጥናትና ምርምር እና ለመሣሰሉት አገልግሎቶች በሚፈልግበት ጊዜ ከአዋሹ ጋር በሚደረግ ሥምምነት በውሰት ሊሰባሰብ ይችላል፡፡
2. በውሰት የተሰባሰበ ቅርስ ለተወሰነ ጊዜ ለዓውደ ርዕይ፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለትምህርትና ለመዝናኛ አገልግሎቶች ሊውል ይችላል፣
3. በውሰት የተሰባሰበው ቅርስ በውሰት የሚቆይበት የጊዜ ገደብ በአዋሹና በተዋሹ ሥምምነትና በቅርሱ የውሰት አስፈላጊነትና ዓላማ ላይ ተመሥርቶ የሚወሰን ይሆናል፣
4. ቅርሱ በውሰት ከመሰብሰft በፊት ሁሉንም የዋስትና ሁኔታዎች በተመለከተ በአዋሹና በስብስብ ማዕከሉ መካከል የውል ሥምምነት መኖር አለበት፡፡ በሥምምነቱም ላይ ኃላፊነቱን የሚወስደው አካል ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡
5. ቅርስ በውሰት የሚሰባሰብበት ዝርዝር አፈፃፀም በቅርስ ውሰት መመሪያ ቁጥር
15/2006 መሠረት ይሆናል፡፡

10. <u>ቅርስን በውርስ ስለማሰባሰብ</u>

1. በአዋጁ አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በተደነገገው መሠረት ማንኛውም በስብስብ ማዕከል የመጠበቃቸው አስፈላጊነት የታመነባቸው ወይም ተገቢው ጥበቃ፣ ጥገናና እንክብካቤ ያልተደረገላቸውን ወይም ለብልሽት የተጋለጡትን ወይም ለሌላ ህገወጥ አገልግሎት የዋሉ ቅርሶችን ባለሥልጣኑ ሊወርስ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘን ወይም ሲዘዋወር የተገኘን ቅርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይወርሳል፡፡
3. አንድ ቅርስ በግለሰብ እጅ ያለ ሆኖ ባለይዞታው ከሞተ እና ሕጋዊ ወራሽ ከሌለው ቅርሱን ባለሥልጣኑ ይወርሳል፡፡

11. <u>ቅርስን በልውውጥ ስለማሰባሰብ</u>

1. በታሪካዊ ወይም በሥነ-ጥበብ ወይም በኢትኖግራፊ ስብስብ ማዕከሎች ውስጥ ቅርሶች እንደየስብስብ ማዕከሉ ዓይነት ከሚፈለገው ቁጥር በላይ ሆነው ሲገኙ ከሌሎች

**የቅርስ ባለይዞታዎች ጋር በሚደረግ ሥምምነት ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና**

የቅርስነት እሴት ያጡትን ስብስቦች አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 10/2006 መሠረት እንዲዛወሩ ተደርጎ በልውውጥ ሊሰበሰft ይችላሉ፡፡

2. ለልውውጥ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የቅርሶች ቁጥር እንደስብስብ ማዕከሉ እና የቅርሱ ባህሪ ታይቶ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መሥፈርት የሚወሰን ይሆናል፤

## 12. ቅርስን በጥናትና ምርምር ስለማሰባሰብ

1. ቅርስ በጥናትና ምርመር መመሪያ ቁጥር 14/2006 መሠረት ፈቃድ በተሰጣቸው የተለያዩ አጥኚዎች በመስክ አሰሳ እና በቁፋሮ ሊሰባሰብ ይችላል፡፡
2. በግንባታ ወቅት በአጋጣሚ የተገኘና በአዋጁ አንቀፅ 41 ድንጋጌ መሠረት አስፈላጊው ሁኔታ የተከናወነለት ቅርስ ሊሰባሰብ ይችላል፡፡
3. ከመስክ በጥናትና ምርምር የሚሰባሰft ቅርሶች ዓይነት በዋነኛነት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

    ሀ. የጥንተ ዓለም ፍጥረት ቅሪተ አካል

    ለ. የአርኪዎሎጂ ቅ

    ሐ. የጥንተ ዓለም የሰው ዘር ቅሪተ አካል

    መ. የሶስዮሎጂና ባህላዊ ሥነ ሰብዕ

## 13. ከውጭ ሀገር የሚመለሱ ቅርሶችን ስለማሰባሰብ፤

1. በተለያዩ ጊዜያት በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር የወጡ ቅርሶችን ከሚገኙባቸው ሀገራት በመመለስ ማሰባሰብ ይችላል፡፡
2. በውጪ ሀገር የሚገኝ ቅርስን በተመለከተ የተገኘው አስፈላጊው የሠነድና ተዛማጅ መረጃ ለሚመለከተው አካል ይተላለፋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መረጃው የተሰበሰበና ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመከተልና ቅርሱ ከሚገኝበት ሀገር መንግሥት ጋር ግንኙነት በማድረግ የተመለሰው ቅርስ ወደሚመለከተው የስብስብ ማዕከል እንዲገባ ይደረጋል፣
4. ዋና ቅርሱን ማግኘት ወይም ማስመለስ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ቅጅውን በማሠራት የሚመለስበት መንገድ ይፈለጋል፡፡

## ክፍል
## ሦስት

## የሚሰበሰf t ቅርሶች መመዘኛ መሥፈርቶች

### 14.ታሪካዊ ቅርስን ለማሰባሰብ መመዘኛ መሥፈርት

መረጃ ያላቸው፣ በታሪካዊ ይዘታቸው የጐላ ድርሻ የሚያበረክቱ ሆነው፡-

1. ከቁፋሮ ውጭ የተገኙና ቀደምትነት ያላቸው ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሐስ ወይም ከሌሎች ቁሶች የተሰሩ ገንዘቦች፣
2. በተወሰነ የታሪክ ወቅትና ሁኔታ በሀገራዊ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተፈፀሙ ክንዋኔዎች በሀገራት መሪዎች፣በጦር አበጋዞች፣ በሃይማኖት አባቶች፣ በጠቢባንና በሌሎችም ታላላቅና ታዋቂ ሰዎች ዘንድ አገልግሎት ላይ የዋሉና ለተፈፀመው ክንዋኔ በአስረጅነት መወሰድ የሚችሉ፣
3. ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሐስ ወይም ከሌላ ቁስ የተሠሩ ሆነው ረዘም ያለ ዕድሜ ያላቸው የነገሥታት ወይም የሃይማኖት መሪዎች ወይም የሌሎች ታላላቅ ሰዎች ስም ወይም ምሥል የተቀረፀባቸው እንደ ዕናዕል ወይም ሰን ወይም ብርት ወይም መስቀሎች ወይም ሥዕሎች ወይም የመቋሚያ መጨበጫዎች ወይም አትሮንሶች የመሳሰሉት ፣
4. ከውጪ ሀገር መንግሥታት ወይም የልዑካን ftድኖችና ከመሣሰሉት ለኢትዮጵያ ታላላቅ ሰዎችና ልዩ ልዩ ተቋማት የተበረከቱ የወዳጅነት፣ የክብርና የመታሰቢያ ዕቃዎች፣

በታሪካዊ ቅርስነት ይሰበሰባሉ፡፡

### 15. የብራና መጻሕፍትን በቅርስነት ለማሰባሰብ መመዘኛ መሥፈርት

ማንኛውም

1. ከብራና የተዘጋጀ መጽሐፍ፣ በስድ ንባብ ወይም በግጥም በአማርኛ ወይም በግዕዝ ወይም በአረብኛ ወይም በሌሎች ቋንቋዎች ተጽፎ የሚገኝ ጽሑፍ፣
2. እንደመጽሐፍ የተጠረዘ የአስማት ወይም የሥዕል ጽሑፍ ወይም ስንክሣር፣

3. በብራና ላይ የተጻፉ ታሪካዊ ሰነዶች ወይም ክታቦች ወይም ገድሎች ወይም ዜና መዋዕሎች ወይም ሌሎችም የሐረግ ጌጥና ሥዕል ያለባቸው ጽሑፎች

4. ቀደም ሲል ያልተለመደና አዲስ የብራና ሥራ ውጤት

የሆነ፡፡ በብራና መጻሕፍት ቅርስነት ይሰበሰባል፡፡

## 16.የሥነ ጥበብ ቅርስን ለማሰባሰብ መመዘኛ መሥፈርት

ማንኛውም

1. መሠረታዊ የሆነ የሥነጥበብ አሠራር ክህሎትን የተከተለ ሥዕል ወይም ቅርፅ፣
2. ሥዕሉ ወይም ቅርፁ የተሠራበት ቁስ ዓይነትና ጥራቱ የቆይታ ጊዜውን ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የማይደበዝዝና የማይሰበር
3. ከመጽሔት ወይም ከመጽሐፍ ላይ ኮፒ ሆኖ ያልተሠራና በራስ ፈጠራ ላይ ብቻ የተመሠረተ፣
4. የሥነጥበft ድርሰት ቅንብር ወጥና ትውልድ ተሻጋሪ ሆኖ በግራፊክስ ወይም በሐውልት ወይም በሚዩራል ወይም በሚክስድ ሚዲያ ወይም በባህላዊና ዘመናዊ ቀለም ቅብና አሣሣል ወይንም በማንኛውም ዓይነት መንገድ የተሠራ፣
5. የብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦችን ባህል፣ ሃይማኖት፣ልማዳዊና ባህላዊ ዕምነቶች በጎ ገፅታን የሚያንፀባርቅ ወይም ለዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከቱ ግለሰቦች ተግባር ውጤት የሆነ፣
6. የባለሙያው ስም፣ የተሠራበት ቁስ፣ የተሠራበት ዘመን፣ የመሳሰሉት መረጃዎችን አሟልቶ የያዘ፣

ሥራ በሥነ-ጥበብ ቅርስነት ይሰበሰባል፡፡

## 17. የኢትኖግራፊ ቅርስ ለማሰባሰብ መመዘኛ መሥፈርት

የኢትኖግራፊ ቅርሶች የሀገራችንን ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ማንነት ፣ ታሪክ ፣ ባህል ፣ ዕምነት ፣ ወግ ፣ ልማድ፣ አመለካከት ፣ አኗኗር ገላጭ የሆኑና በኅትመት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የተዘጋጁ ወይም በቁስ የሚገኙ ሆነው፡-

1. የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች፣

2. አልባሳትና ጌጣጌጦች፣

3. የጦርና የአደን መሣሪያዎች፣

4. የሙዚቃና የሙዚቃ መጫዎቻ መሣሪያዎች፣
5. የዕደ ጥበብ ሥራ ውጤቶች፣
6. ሃይማኖታዊ ፣ባህላዊና ልማዳዊ የበዓላት መከወኛ ቁሳቁሶች፣
7. የማምረቻ መሣሪያዎች፣

የሆኑ በኢትኖግራፊ ቅርስነት ሊሰባሰft ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

19. **ቅጣት**

ይህን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

20. **ተፈፃሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ይህ መመሪያ በሸፈናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

21. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

22. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡